የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥረኛ ዓመት ቁጥር ፳፪
አዲስ አበባ ጥር ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

10th Year No. 22
ADDIS ABABA-27th January, 2004

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፹፯/፲፱፻፺፮ ዓ.ም
ለአርብቶ አደር አካባቢዎች ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከዓለም ዐቀፍ ግብርና ልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ............. ገጽ ፪ሺ፭፻፵፬

## CONTENTS

Proclamation No. 387/2004
International Fund for Agricultural Development Loan for Financing the Pastoral Community Development Project Ratification Proclamation ............................ Page 2544

## አዋጅ ቁጥር ፫፻፹፯/፲፱፻፺፮

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ ግብርና ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለአርብቶ አደር አካባቢዎች ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ኤስ.ዲ.አር ፲፬ሚሊዮን፬፻ሺ (አሥራ አራት ሚሊዮን አራት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ ግብርና ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ኦክቶበር ፲ ቀን ፪ሺ፫ በሮም የተፈረመ በመሆኑ፤

መሠረታዊ የኤኮኖሚ ዓለም ዐቀፍ ውሎች ተፈጻሚ ከመሆናቸው በፊት መፅደቅ ስላለባቸው፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭/፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION NO. 387/2004.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL FUND FOR AGRICULTURAL DEVELOPMENT

**WHEREAS**, a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Fund for Agricultural Development stipulating that the International Fund for Agricultural Development provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of SDR 14,400,000.00 (Fourteen Million four Hundred thousand Special Drawing Rights) for financing the Pastoral Community Development Project, was signed in Rome on the 10th day of October, 2003;

**WHEREAS**, basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

**WHEREAS**, The House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Loan Agreement at its session held on the 27th day of January, 2004;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution it is hereby proclaimed as follows:

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ለአርብቶ አደር አካባቢዎች ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከዓለም ዐቀፍ ግብርና ልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፫፻፹፯/፲፱፻፺፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

፪. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ ግብርና ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ኦክቶበር ፲ ቀን ፪ሺ፫ በሮም የተፈረመው ቁጥር 612-ET የብድር ስምምነት ነው::

፫. <u>የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ኤስ.ዲ.አር ፲፬ሚሊዮን፬፻ሺ (አሥራ አራት ሚሊዮን አራት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል::

፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከጥር ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ጥር ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "International Fund for Agricultural Development Loan for Financing the Pastoral Community Development Project Ratification Proclamation No. 387/2004."

**2. Definition**

In this Proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement No. 612-ET signed in Rome on the 10th day of October 2003 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Fund for Agricultural Development.

**3. Power of the Minister of Finance and Economic Development**

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of SDR 14,400,000.00 (fourteen Million four Hundred Thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**3. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the 27th day of January, 2004

**Done at Addis Ababa, this 27th day of January, 2004**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**